# “ኦፕሬሽን ፎርቶ” እንዴት ከሸፈ?፣ አቶ ኢሳያስስ ምን አሉ?

**ዘአማን በላይ** bzaman@yahoo.com

ጊዜው ምናልባትም ከዛሬ አራት ወራት በፊት ይሆናል። በኤርትራ ሠራዊት ውስጥ አዲስ የነፃነት ጥያቄን ያነገቡ ወታደሮች በህቡዕ እየተወያዩ ነው። ወይይታቸውም ህገ–መንግስት የሚታወቀውና በአንድ ሰው ይሁንታ በምትዘወረው በዚያች ትንሽዬ ሀገር ውስጥ የዴሞክራሲ ጭላንጭል እንዲታይ የሀገሪቱን ሙሬ በማያዝ ማከፈፀም እንደሆነም ተስማምተዋል— ጥቂት መኮንኖችና ወታደሮች። በወቅቱ የዚህ ክንዋኔ ዘመቻ ስም ባይወጣለትም ከተግባሩ ፍፃሜ ጋር ተያይዞ በቅርቡ “ኦፕሬሽን ፎርቶ” የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፤ ዘመቻው ተጀምሮ በተጠናቀቀበትና የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ህንፃ የሚገኝበትን ቦታ ለማጠቆም በሚል።

መቼም የዛሬው ፅሑፌ ዓላማ የዘመቻውን ስያሜ አስመልክቶ ሃሳቦችን ማንሸራሸር አለመሆኑን ወድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡት ተስፋ አደርጋለሁ። በመሆኑም በዚህ መጣፊ “ኦፕሬሽን ፎርቶ” እንደምን ከሸፈ?፣ የዘመቻው ወሸንፍር ሰለባ ሊሆኑ የነበሩት ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂስ ከሶስት ሳምንታት ዝምታ በኋላ ምን አሉ? የሚሉ ያልተዳሰሱ ጥያቄዎችን በማንሳት አንባቢዎቼ ስለ ዘመቻው የአከሻሸፍ ሁኔታ በቅድሚያ አወጋችኋለሁ። ለጥቄም ወዲ አፎም ሶስት ሳምንት ሙሉ እምጥ ይግቡ ስምጥ ሳይታወቅ፣ በራሳቸው ማናኛ ብዙሃን እንደ ማስቀል ወፍ ድንገት ብቅ ብለው የተናገሩትን አስገራሚ ዲስኩር ከዕውነታው ሰበዝ ጋር በማማከር ላስቃኛችሁ እሞክራለሁ። መልካም ንባብ።

ከዛሬ አራት ወራት በፊት የተጠነሰሰው “ኦፕሬሽን ፎርቶ” እምብዛም ያልተቀናጀ እንዲሁም በዘመቻው እንሳተፋለን ያሉ የኤርትራ ሜካናይዝድ ክፍለጦሮች ባልታወቀ ምክንያት የተንሸራተቱበት እንደነበር የ“ኣሰና ዶት ኮም” የሚዲያ ምንጮች ይጠቁማሉ። ይሁንና እነዚህ ጉድለቶችን አንግቦ ከፆረና ግንባር እስከ ፎርቶ ድረስ የተመመው ይህ ዘመቻ፤ ስልጣን ላይ ላለውና ከስያሜው ጋር አንዳችም ግንኙነት ለሌለው “ህግደፍ” (ህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ለፍትሕ) ለተሰኘው ሻዕቢያዊ ቡድን የማስጠንቀቂያ ደወል መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይመስለኝም። እስቲ ለማንኛውም “የኦፕሬሽኑን” አጀማመርና ፍፃሜ በቅደም ተከተል እንዲህ እንመልከት።...

...በምስጢር ወይይት ያደረጉት መኮንኖችና ወታደሮች አመቺ ጊዜን እየተጠባበቁ ነው። እናም አቶ ኢሳያስን ለማግኘት አንድ ወጥ የሆነ ወቅትን አድብተው ሲጠባበቁ ሰንብተዋል። መቼም አመቺ ቀን ሚፈጠሩ የግድ ነውና ከመሰንበቻው እንዲህ ሆነ።... በዚያን ሰሞን አቶ ኢሳያስ ፎርቶ በሚገኘው የማስታወቂያ ሚኒስቴር አዳራሽ ወስጥ ከዞን አስተዳዳሪዎች ጋር ስብሰባ ተቀምጠዋል—ኦፕሬሽኑ ሊካሄድ ሶስት ቀናት ሲቀሩት፤ ዕለተ–ዓርብ ላይ። የዕለቱ ስብሰባ እስከ ዓርብ አሜሻሹ ድረስ ሊጠናቀቅ ስላልቻለ ስብሰባው እዚያው አዳራሽ ወስጥ ሰኞ ጠዋት ሶስት ሰዓት ላይ “ሀገር ሚዲያ” እየተባለ በሚጠራው የማስታወቂያ ሚኒስቴር አዳራሽ ወስጥ እንደሚቀጥል አቶ ኢሳያስ ይናገራሉ።

ይሁንና የስብሰባው ተካፋይ የነበሩትና የደቡባዊ ዞን አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ ማስጠፉ ኑርሁሴን ይህን ሚሺጃ ለአሜሁ ሜዎች አሾልከው ሹክ ይላሉ— ሰኞ ዕለት ሚኒታውቂያ ሚኒስቴር አዳራሽ ወስጥ ስብሰባው ስለሚቋጥል ያሰቡትን ሚፀም እንደሚቿሉ በማጠቆም። እርግጥ የሰኞወን አሜፅ ከሜኑት ከእነ ብርጋዲየር ጄኔራል ሳልህ አስማን ሜክናይዝድ ክፍለጦር በስተቀር፤ ከሌሎች የጦር ክፍሎች የተወጣጡና ኦፕሬሽኑን የሚጂግፋት እንዲሁም በአሜሁ ለሚተፍ ለተዘጋጁት ሜክናይዝድ ክፍለ ጦሮች የተነገራቸው ነገር አልነበረም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ባልተለሜደ ሁኔታ የስብሰባወን ቦታ አስቀድሜው በሚገራቸው ጥርጣሬ ስላደረባቸወና በዘሜቻው ለሚተፍ የወሰኑ ክፍሎችም ይህን ከሰሙ ክንዋኔወን ለሌላ አሜቺ ጊዜ እንቀይረው ይሉናል ከሚል ስጋት የሚጨሊሆን ይችላል።

ያም ሆነ ይህ ግን፤ እሁድ ከሰዓት በኋላ ሁለት መቶ የሚሆኑ መኮንኖችና ወታደሮች ታንኮችንና የታጠቁ ተሽከርካሪዎችን በሜያዝ ወደ አስሜራ ማቅናት ጀሜሩ—በ"ኦፕሬሽኑ" ማንኛወንም ዋጋ ለሜክፈል በመወሰን። ከኢትዮጵያ ጋር በስተደቡብ ከሚዋሰነው የፆረና ግንባር የሜጠትና በዘሜቻው ለሜካፈል የወሰኑት እነዚህ የሰራዊት አባላት፤ ሰኞ ጠዋት 12 ታንኮችን ይዘው ከአስሜራ 40 ኪሎ ሜቱር ርቀት ላይ ደቀሜሐሪ ከተማ ደረሱ። ታዲያ በጉዟቸው ወቅት ነዳጅ ጨርሰው ስለነበር ለመሙላት ፈለጉ። ይሁንና በቅፅል ስማቸው "ወልዱ ባርያ" እየተባሉ በሚጠሩት የሰራዊቱ አዛዥ ስር ከነበረው የነዳጅ ሚዲያ ጣቢያ ነዳጅ መቅዳት እንደሚይችሉ ይነገራቸዋል።...በስተሜጨረሻ ግን ወታደሮቹ ኃይል ለማጠቀም ስለተገደዱ በግዳጅ ነዳጅ ይቀዱና ጉዟቸወን ወደ አስሜራ ያደርጋሉ። ጊዜ የለም።

አቶ ኢሳያስን ፎርቶ ላይ ለሜያዝ የተጣደፉት ወታደሮቹ ደቀሜሐሪ ላይ አንድ ታንክ በብልሽት ምክንያት ቢቆምባቸወም ቀሪዎቹን ታንኮችና የታጠቁ ተሽከርካሪዎችን በሜያዝ ፊት ለፊት ማስገሳቸወን ተያያዙት።..."ሚርሓኖ" የሚባል አካባቢ እንደደረሱም ሶስቱ ታንኮች አየር ማንገዱንና አየር ኃይሉን እንዲጠብቁ አድርገው፤ በቀሪዎቹ ወደ ማሃል አስሜራ ዘለቁ— ልክ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ ላይ።... እርግጥ ቀደም ሲል በተያዘ ማኻ ዕቅድ ማስረት ይህን የፆረና ሜክናይዝድ ሃይል ከከረንና ከነፋሲት አካባቢዎች የሚሜጡ ሌሎች ሜክናይዝድ ብርጌዶች ይቀላቀሏቸው ነበር። ዳሩ ግን ባልታወቀ ሁኔታ እነዚህ ብርጌዶች "ኦፕሬሽኑን" ሊቀላቀሉት አልቻሉም።

እናም ኮሎኔል ሰዓድ ዓሊን (ወዲ ዓሊ)፣ ኮሎኔል ዓለምን (ግዛዋ) እና ኮሎኔል ኣብርሃምን (ገላዋ) አቅፎ ከፆረና ግንባር የተንቀሳቀሰወና በብርጋዲየር ጄኔራል ሳልህ አስማን የሚሜራው የሜክናይዝድ ክፍለ ጦር አባላት፤ ገና ደቀሜሐሪ እንደደረሱ ነበር በሌሎች የጦር ክፍሎች ክህደት እንደደረሰባቸው የተገነዘቡት። እናም ምንም ዓይነት አሚራጭ አልነበራቸወም—በፍጥነት የሚኒታውቂያ ሚኒስቴሩን ህንፃና ሰራተኞቹን ከመቆጣጠር በስተቀር።

አስሜራ ከተማ ከደርግ ወድቀት በኋላ እንዲህ ዓይነት የወታደራዊ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴን አስተናግዳ አታውቅም። እናም ይህ ያልተለሜደ የታንኮችና የወታደሮች ሩጫ ነዋሪወን ያስደነገጠ ብቻ ሳይሆን እርስ በርሱ እንዲነጋገር ያደረገ ነው። አብዛኛው ነዋሪም በከተማዋ ወስጥ አንዳች የተለየ ነገር እየተካሄደ ለማሆኑ እርግጠኛ ሆኗል።...አዎ! ወታደሮቹ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ላይ ሚኒታውቂያ ሚኒስቴሩን ተቆጣጥረወታል። የኤርትራ ቴሌቪዥን ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አስሜላሽ አብርሃን በሚስገደድ የፖለቲካ ፍላጎታቸወን እንዲያነቡ አድርገዋቸዋል። ህዝቡም በአቶ አስሜላሽ ድምፅ "የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ እ.ኤ.አ. በ1997 የተረቀቀው ህገ-መንግስት ገቢራዊ ይሁን…." የሚሉ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን አደሜጡ። ግና ከጥቂት ቆይታ በኋላ የኤርትራ ቴሌቪዥን በሜቋረጡ ምክንያት የአሜፅያኑ ሜሉ ጥያቄ ሊሰማ አልቻለም።

እርግጥ እዚህ ላይ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ማንዘብ ያለበት ዕውነታዎች አሉ። እነርሱም የአሜሪያኑም ሆነ ያካሄዱት "ኦፕሬሽን" ዓላማ ሚስታወቂያ ሚኒስቴሩን ማያዝ አሊያም የፖለቲካ ፍላጎታቸውን በቴሌቪዥን ማስተጋባት አልነበረም። ዋነኛ ዓላማቸው ማስታወቂያ ሚኒስቴር አዳራሽ ወስጥ ሰኞ ጠዋት ስብሰባ ያካሂዳሉ የተባሉትን ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂን በአካል ማያዝ ነበር። ሆኖም ኤርትራ ወስጥ የአቶ ኢሳያስ ባለሟሎች ጆሮ ረጅም ስለሆነ ሚጃው ስለደረሳቸው ስብሰባው "ግቢ" እየተባለ የሚጠራው ቤተ–መንግስት ወስጥ እንዲካሄድ አስቀድመው ወስነዋል። ዳሩ ግን አቶ ኢሳያስ በዘመቻው በደንብ ያልታጠቁ ጥቂት ሰዎች እንደሚሳተፉና እነዚህንም ሰዎች በቀላሉ በቁጥጥር ስር እንደሚያውሏቸው አስበው ነበር። ወታደሮቹ ታንና ሌሎች ከባድ መሳሪያዎችን የታጠቁ መሆናቸውን ሲገነዘቡ ግን ከማበል ወጪ አማራጭ እንደሌላቸው ተገንዝበዋል።

አሁን አቶ ኢሳያስና የቅርብ ባለሟሎቻቸው ሜከናይዝድ ብርጌዱ በዘመቻው መሉ ተሳታፊ መሆኑን አወቀዋል። እናም ወታደሮቹን በተለያዩ ዘዴዎች ሊቀርቧቸው ሞከሩ። የተለያዩ ወታደራዊ አዛገቾችንና የሀገር ሽማግሌዎችንም እንዲያግባቡዋቸው ላኳቸው። አልሆነም። በስተመጨረሻም የሜከናይዝድ ስታፍ አዛዥ የሆኑትን ኮሎኔል ፀሐዬ መኮንን (ወዲ ሞኬን) ላኳቸው። ግና አንድ ክስተት ማከል ላይ ተፈጠረ።....ነገሩ እንዲህ ነው።...

...በወቅቱ ክላሽንኮቭ መሳሪያና ሽጉጥ ይዘው የነበሩት ኮሎኔል ሰዒድ ዓሊ (ወዲ ዓሊ) ድንገት ግስላ ይሆናሉ። እናም መሳሪያቸውን አነጣጥረው አራት ጥይቶችን በመተኮስ ኮሎኔል ፀሐዬን ያቆስሏቸዋል። በዚህም አላበቁም። ፕሬዚዳንት ኢሳያስ እንደሚይያዙ ያወቁት ኮሎኔል ሰዒድ ታንኮቹ ወደ ቤተ–መንግስት እንዲቱሱ ያዛሉ። ይሁንና ጓደኞቻቸው በትዕዛዙ ይደናገጣሉ። ጓደኞቻቸው ላለመተኮስ ሲያቅማሙ የተመለከቱት እኚህ ኮሎኔል፤ የታንኮቹን አፈሙዞች ወደ ቤተ–መንግስቱ አነጣጥሩልኝና እኔ ራሴ እተኩሳለሁ ይሏቸዋል።

ታዲያ በዚህ ወቅት ነበር— የአቶ ኢሳያስ የቀኝ እጅ መሆናቸው የሚነገርላቸው ብርጋዲየር ጄኔራል ኢዮብ (ሓለባይ) እና በአቶ ኢሳያስ ከቁብ የሚቆጠሩት የመከላከያ ሚኒስትሩ ጄኔራል ኤፍሬም ስብሃት "እባካችሁ በሰሜታት ይሁንባችሁ" በማለት፤ የአሜሪያኑ ፍላጎት የራሳቸው መሆኑን በመግለፅ ሊያግባቧቸው የሞከሩት። እናም በዕለቱ ለዓይን ያዘ ሲያደርግ ድርድርና ክርክር በሁለቱም ወገኖች መካከል ተካሄደ። አማፂያኑ እንደሚታሰሩ ቃል ተገባላቸው። በድርድሩ መሰረትም አሜሪያኑ የማስታወቂያ ሚኒስቴሩን ህንፃና ሰራተኞቹን ለቀቁ።

ኋላ ላይም ብርጋዲየር ጄኔራል ሳልህ ኦስማን፣ ኮሎኔል አብርሃም (ገላዋ)፣ እና (ወዲ ዓሊ) ከአስመራ በስተምዕራብ በኩል ወደምትገኘው "ቑሸት" ወደተሰኘች ቦታ ለመሄድ ይወስናሉ። መፈናፈኛ ግን አላገኙም። ሲለምንና ሲያስለምን የነበረው የአቶ ኢሳያስ ቡድን ግን ይከባቸዋል። ከወዲ ዓሊ በስተቀር ዋነኛዎቹ የኦፕሬሽኑ አዛገቾች ማለትም ብ/ጄኔራል ሳልህ ኦስማን፣ ኮሎኔል ኣብርሃም (ገላዋ) እና ኮሎኔል ዓለም (ግዛዋ) ተይዘው ታሰሩ።...እናስ የወዲ ዓሊ ዕጣ ፈንታ ምን ሆነ?...

አዎ! ኮሎኔል ሰዒድ ዓሊ ከከበባው በማምለጥ "ሽበቕ" ወደሚባል ቦታ ይደርሳሉ። ይሁንና እዚያም ቢሆን መከበባቸውን ለማንዘብ ጊዜ አልወሰደባቸውም። እናም በአራት የአቶ ኢሳያስ ከባቢ ወታደሮች ላይ የተኩስ እሩምታን በመክፈት አቆሰሏቸው። አቶ ኢሳያስ አፈወርቂን እጅ ከፍንጅ ለማያዝና ከእርሳቸው ጋር ፊት ለፊት ለመደራደር ፎርቶ የሄዱት እኚህ ኮሎኔል እጃቸውን ለመስጠት አልፈለጉም። ግራ ጎናቸው ላይ የሻጠቱን ሽጉጥ ከመቅፀፈት ላጥ አድርገው በማውጣት አፈሙዙን ግንባራቸው ላይ ደቅነው ቃታውን ሳቡት። እናም እንደ ኢትዮጵያዊው አፄ ቴዎድሮስ ለሀገራቸው ህዝብ ሲሉ እስከወዲያኛው አሸለቡ። ከወዲ ዓሊ ሞት በኋላም ከዘመቻው ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉትና የረጅም ጊዜ የሻዕቢያ ድርጅታዊ ጉዳይ ኃላፊ ሆነው የሰሩት አቶ አብደላ ጃበር እንዲሁም የደቡባዊ ዞን አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ሙስጠፋ ኑርሁሴን አፈ–

ሰፊዎቹ የሻዕቢያ እስር ቤቶች እንዲወጣቸው ተደርጓል። በስተሜጨሻም "አፕሬሽን ፎርቶ" እንዲህ ከሸፈ።...

ታዲያ እዚህ ላይ 'አቶ ኢሳያስ ኦፕሬሽኑን አስሜልከተው ምን አሉ?' የሚል ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። አዎ! ይህን በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ አካላትን ተግባር አቶ ኢሳያስ ከሶስት ሳምንት ዝምታ በኋላ በተለመዶ ቅጥፈታቸው አጣጥለውታል። ፕሬዚዳንቱ ከኤርትራ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ የአሜፀያኑን የፍትህና የዴሞክራሲ ጥያቄን "ከምንም የማይቆጠር አጋጣሚ" በማለት ከገለፁት በኋላ ፤ "የተያዘወም ተይዞ ፣ ራሱን ያጠፋውም አጥፍቶ ፊልሙ ተጠናቅቋል" ሲሉ ተደምጠዋል። ይህ ብቻም አይደለም፡ "የአብዬን ወደ እምዬ" እንዲሉት ዓይነት ምክንያትን አሰምተዋል። ይኸወም ለሶስት ሳምንታት ያህል መንግስታቸው ስለ አመፁ ትንፍሽ ያላለበትን ምክንያት ሲያስረዱም "የወሸት ተናጋሪዎችን ወሸት የመናገር መብትን ለማክበር ነው" በማለትም ለማላለቅ ሞክረዋል።

ታዲያ እዚህ ላይ እነዚህን የሰወዬወን አባባሎች ከኦፕሬሽኑ እንዲሁም ከሻዕቢያና ከእርሳቸው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሜፈተሽ ተገቢ ይመስለኛል። በዚህ ፅሐፍ አቅራቢ እምነት፤ በአሜፀያኑ የተካሄደው ዘመቻ አቶ ኢሳያስ እንዳሉት ከምንም የማይቆጠር አጋጣሚ አይደለም፡ ቀደም ሲል ከኦፕሬሽኑ እንደተረዳነው ዓላማው እርሳቸውን በአካል ለማያዝ ያለመ በመሆኑ ቢያንስ የአሰራር ለወጥ ሊያመጣ የሚችል በመሆኑ ነው። ከዚህ ባሻገርም የአንድ ሀገር ሜሪ ከምንም ለማይቆጠር አጋጣሚ ጊዜ ይዞ፣ ተዘጋጅቶና ህዝቡ እንዲከታተለው አድርጎ መግለጫ ሊሰጥ የሚችልበት ምንም ምክንያት ሊኖረው ስለማይችል ነው።

ያን ያህል የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ቀልብ ስቦ የነበረ ትዕይንትን በአጋጣሚነት እንደተከናወነ አድርጎ ሜረጅ "ዓይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ" የሚል የተለመዷ የአስመራ መንግስት ጨዋታ ነው። ለምን ቢሉ "ኦፕሬሽኑ" ስጋና አጥንት ለብሶ የታቀደው ከዛሬ አራት ወራት በፊት በመሆኑ ይህን ሻዕቢያዊ ያረጀ ያፈጀ ጨዋታ ገሃድ ያወጣዋልና። እርግጥ አቶ ኢሳያስ ይህን ማለታቸው ምናልባትም ህዝባቸውን ለማረጋጋት አስበው ከሆነ፤ ማለፊያ ዘዴ አይመስለኝም፡ ምክንያቱም የአሜፀያኑ ጥያቄዎች ዴሞክራሲንና ፍትህን የኤርትራ ህዝብ እንዲያገኝ በመሆኑ፤ የዚያች ሀገር ወንድም ህዝብ 'እኛ ዴሞክራሲንና ፍትህን አንፈልግም' ሊላቸው ስለማይችል ነው።

ለነገሩ የአቶ ኢሳያስ ፍላጎት ግልፅ ነው—ዛሬም የስቃይ ቀንበርን የሚሸከም ዜጋ እንዲኖር ይፈልጋሉና። ህዝቡ ግን ከአብራኩ በወጡ ልጆቹ አማካኝነት የእርሳቸው አገዛዝ የመሚረወና የቸከው መሆኑን እየነገራቸው ነው። ምናልባት የዚህ ፅሐፍ አንባቢ 'የኤርትራ ህዝብ ለምን አቶ ኢሳያስን እንዲህ ያመርባቸዋል?' የሚል ጥያቄ የሚያነሳ ከሆነ ዕወነታውን እንካችሁ ልበል።...

እርግጥም የአስመራውን ፈላጭ ቆራጭ አስተዳደር አገዛዝ በገዛ ህዝቡ ላይ የግፍ ቀንበርን ከጫነ 21 ዓመታት አልፈውታል። ይህ ሁኔታም ኤርትራ ወስጥ በሻዕቢያ ላይ የሰላ ሂስ የሚሰነዝሩ ዜጎች፣ የሃይማኖት አባቶችና በተቃዋሚነት የተሰለፉ ኤርትራወያን ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያሻቅብ አድርጎታል፡፡ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደርም ይህን ሁኔታ ለማዳፈንና የጸረ-ዴሞክራሲያዊነት ሰሱን ለመወጣት በየጎጡ እስር ቤቶች ከፍቶ ኤርትራን የእሥር ቤቶች ሰንሰለት በማድረግ ሀገሪቱን "ወደ ትልቅ እስር ቤትነት" እየቀየራት ነው፡፡

አዎ! ሀገረ – ኤርትራ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የእምነት ነጻነት የሌለበት ብቻ ሳትሆን፣ በሻዕቢያ ጦረኛና ፀረ –ዴሞክራሲያዊ ጠበል ያልተጠመቁ ጋዜጠኞች እንዲሁም ትላልቅ የሃይማኖት አባቶች በየማጎሪያዎቹ ወደ ተገነቡት የእስር ቤት ሰንሰለቶች የሚወረወሩባት ሀገር ጭምር ናት፡፡ በቃ ዜጎች እስከወዲያኛው ሃሳባቸውን እንዳይገልጹ፣ ሃይማኖታቸውን በአደባባይ እንዳያከብሩ ፀጥ ይላሉ – የአቶ ኢሳያስን የግፍ በትር በመፍራት፡፡ እናም የዴሞክራሲም ይሁን የፀሎት ድምጻቸው ሳይሰማ ጸጥ ይላል፡፡ ፀጥታወም በእስር አሊያም እስር ቤቶች ወስጥ በሚደረግ አሰቃቂ ግድያ ይደመደማል፡፡ እንደ ሰንሰለት የተያያዙት የሻዕቢያ  እስር ቤቶችም የራሳቸውን ዜጎች  ግዳይ ይጥላሉ፡፡

...አዎ! በኤርትራ ልሳነ – ምድር የዴሞክራሲና የሃይማኖት  ነጻነት ታፍነው አምባገነንነትና ፀረ – ዴሞክራሲያዊነት "ሮጬ" እየረገጡ ነው – እስር ቤቶቹ ደገሞ የአቶ ኢሳያስንና እፍኝ የማይሞሉ ተከታዮቻቸውን ፍላጎት ሚርኪያ "የምስጢር ከስ"  ሆነዋል፡፡ ሚጃዎች እንዲያመላክቱት፣ በትንሿ ኤርትራ ወስጥ በግልጽ የሚታወቁ ከ37 በላይ እስር ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ይህም ፀረ – ዴሞክራሲው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በአንድ ወቅት እህል በማምረት "ሲንጋፖርና ታይላንድ ትሆናለች" ያላትን ሀገር ወደ "እስረኞች ማምረቻነት" እየቀየራት መሆኑን በግልጽ  የሚያመላክት  እውነታ ነው፡፡

የሚሌኒየሙ የልማት ግብ ሙሉ ለሙሉ የሚያሳካው የሀገራችን ልማታዊ መንግስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንና የጤና ኬላዎችን በየመንደሩ ሲከፍት፣ አስገራሚው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ግን በየመንደሩ አዳዲስ እስር ቤቶችን ይገነባል፡፡ ያስፋፋል። እኔ የምላችሁ እኚህ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚሊየሙ የልማት ግብ የሚያሳኩት እስር ቤቶችን ለሁሉም ዜጋ በማዳረስ ነው እንዴ?...ወቸው ጉድ!...

ከፍተኛ ግፍ  ከሚፈጸምባቸው ከእነዚህ እስር ቤቶች ወስጥ እስር ቤቶች ወስጥ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ አደርሰር (ሳዋ)፣ ዓዲ ቀይህ፣ ዳህላክ ከቢር (ዳህላክ ደሴቶች) ኢራኢሮ (በአስመራና በምጽዋ መካከል)፣ ጋልዓሎ (ቀይ ባህር ዳርቻ) እና ሓዲሽ ማዓስከር (ሱዳን ጠረፍ አቅራቢያ) ይገኙባቸዋል፡፡ በሀገሪቱ በግልጽ ከሚታወቁት  ከ37 በላይ እስር ቤቶች መካከል በምሳሌነት የጠቀስኳቸውን የእነዚህን አስር ቤቶች ጭካኔ የተሞላበትን አሰራር፤ እርግጥም ሻዕቢያ "እጁን በእጁ የሚበላ" ምን ዓይነት ፀረ – ህዝብ ቡድን መሆኑን አፍ አወጥተው የሚናገሩ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው "የኦፕሬሽን ፎርቶ" ተዋንያን እስር ቤቶቹን አምርረው ከመጥላት ባሻገር፤ በየማጎሪያዎቹ የሚገኙት የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ የጠየቁት። እናም አቶ ኢሳያስ በአጋጣሚነት የጠቀሱት የዘመቻው ተግባር የህዝቡን ሁለት አስርትን የዘለለ ብሶት የሚያመላክት እንጂ ተናንቆ የሚታይ አለመሆኑን ማንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል።

አቶ ኢሳያስ ሌላኛው ያነሱት ነጥብ ለሶስት ሳምንታት ዝም ያልነው የወሽታሞችን ወሽት የሚናገር መብት ለማጠበቅ ነው የሚለው አስቂኝና አስገራሚ አባባል ነው። እስቲ እዚህ ላይ ጥቂት ጥያቄዎችን

ላንሳ።… ዕወን ወሸት ተናጋሪወና ዓይኔን ግንባር ያድርገው የሚል ዲፕሎማሲን የሚጠቀመው ማነው? ኧረ ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው የኤርትራ መንግስት የሰዎችን የመናገር መብት ማክበር የጀመረው?...መቼም "ውቸው ጉድ" እንጂ ሌላ ምን ይባላል?...

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያወቀው የኤርትራ መንግስት ከወሸት ጋር የካቶሊክ ጋብቻ የፈፀመ ነው። ሊፋታ አይችልም። እንዲያውም በሚህ ደረጃ ወሸትን እንደ ትክክለኛ መንገድ የሚከተል ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ አኳያ በርካታ አብነቶችን ማንሳት ቢቻልም፤ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል በሐሰት ከየመን ጋር ሃኒሽ ደሴት ይገባኛል በማለት ጦርነት ቀስቅሶ በፍርድ ቤት ሚረታቱ፣ በኢትዮ–ኤርትራ ጦርነት ወቅት "ታንኮቼ ሳር ሊያጭዱ ነው ባድመና አከባቢዋ የገቡት ማለቱ፣ ራሳቸው አቶ ኢሳያስ የጂቡቲን ራስ ዱሜራ ኮረብታዎች ወርረው ለአደራዳሪዋ ኳታር ጋዜጠኛ በአንድ ወቅት "…ትሰማኛለህ?! በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠ መግለጫም ሆነ ማስታወቂያ የለም፤ …ምንም ዓይነት ግጭት አልነበረም ስትባል፤ አልነበረም ማለት ነው፡፡ አይገባህም እንዴ?!..." ማለታቸው፣ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማስረጃ አስደግፎ ከባቢውን ታምሳለህ እንዲሁም እንደ አል–ሸባብ ያሉትን አሸባሪዎች ትረዳለህ ሲላቸው ሽምጥጥ አድርገው መካዳቸው…ወዘተን መጥቀስ ከዕውነታው በር ያደርሰናል። የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ከወሸት ጋር የቆረበ ስለመሆኑ።

እርግጥ አቶ ኢሳያስ ወሸትን አስሚልከተው ስለ መብት ማውራታቸው በራሱ የሰወዬውን የተለመዷ ባህሪያዊ ማንነትን ለመማዘን ተጨማሪ ዕድል የሚሰጥ ይመስለኛል። ምክንያቱም እርሳቸው "መብት" የሚለውን ቃል ከቃልነቱ በዘለለ ግብራዊ እሳቤውን ስለሚያወቁት ነው። ታዲያ ይህን የዜጎችን የመብት ጥበቃ ከአቶ ኢሳያስ ባህሪ አኳያ ስንመዝነው በአንድ ወቅት አስመራ በነበሩት የአሜሪካ አምባሳደር ተቀነባብሮ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ማስሪያ ቤት የተላለፈውንና ኋላ ላይም አፈትልኮ ወጥቶ ለዓለም ህዝብ "ዊክሊክስ" በተባለ ድረ – ገጽ አማካኝነት ይፉ የሆነውን "የኤርትራ ብርቱ ምስጢሮች"ን በጥቂቱ ማስታወስ የግድ ይለናል። እንዲህም ነበር።…

...አቶ ኢሳያስ ግራ የሚያጋቡ ፍጡር ናቸው፡፡ ግለሰቡ "ያናድዳቸዋል" ተብሎ በሚታሰብ ነገር ላይ ከት ብለው ይስቃሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ "የሚያስቅ" ነገር ሲሰሙ ፊታቸውን በመከስከስ በንዴት የሚጀዙትንና የሚጨበጡትን ያጣሉ፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅት አጃቢዎቻቸው የዋዛ እንዳይመስሏችሁ፡፡ አስቀድሞ የተነገራቸው ይመስል የንዴታቸው መንስዔ የሆነውን ግለሰብ እያዳፉ ወደ ዘብጥያ ይወረውሩታል፡፡

ዘብጥያ የተወረወረው ሰው ነገ በህይወት ስለማኘቱ ማንም ርግጠኛ ባይሆንም፤ አቶ ኢሳያስ ግን በአጃቢዎቻቸው ድርጊት ብቻ የሚረኩ አይደሉም–ደግመው ደጋግመው እጃቸውን እያወናጨፉና ሚልሰው እያፋተጉ በንዴት ይጦፋሉ፡፡…ሰወዬው በደም ፍላት የሚወስኑት ወሳኔያዎች የአንድ ሀገር ፕሬዚዳንት ተግባራት አይመስሉም፤ በሚወስኗቸው ጉዳዮች ላይ አብዛኛውን ጊዜ ሲያማዝኑ አይታዩም፡፡ አንዳንዴ ወሳኔያቸው

ማጠጥ ጠጥቶ ብይን የሚሰጥ ዳኛ አይነት ነው፡፡ አስገራሚም፡ አሳዛኝም፡፡ ስለዚህ መብትን ያለማክበር አባዜና ፀረ- ዴሞክራሲያዊነት የፕሬዚዳንቱ ስር የሰደደ ባህሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡ …

እንግዲህ ይህ በአምባሳደሩ የተገለፀው ዕውነታ የሚያመላክተን ነገር ቢኖር አቶ ኢሳያስ እንኳንስ ስለ መብት ሊናገሩ ቀርቶ ጉዳዩን እንደ ተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ የሚፈሩት መሆኑን ነው። እናም የእርሳቸው ሰሞነኛ በዘመቻው ዙሪያ ያደረጉት ቃለ-ምልልስ "ሰይጣን ላሙ ከመፅሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል" እንዲሉት ዓይነት መሆኑን ማንዘብ ያሻል። ቢጨምቅ ጠብታ ዕውነት የማይወጣውም ጭምር።

እርግጥ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ 'የከሸፈው ኦፐሬሽን ተሳታፊዎች ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆ ይችላል?' የሚል ጥያቄ ሊያነሳ ይችላል። ለምላሹ ግን ብዙ ርቀት ተጉዞ ማሰብ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። እኔም በግሌ ልመልሰው አልችልም። ግና የዊኪሊክስን ሚሼጀ ደግሞ መመልከት የምላሾች ሁሉ ምላሽ ይመስለኛል።…. በአምባሳደሩ የተፃፈው የአቶ ኢሳያስ ማንነት እንዲህ ይላል።….

"….ሰውዬው በተለይም በስልጣናቸው ላይ የመጣ አሊያም ከእርሳቸው ሃሳብ የተለየ አመለካከት በያዘ ግለሰብ ወይም ባለስልጣን ላይ የሚወስዱት ርምጃ የሚጨረሻውን ነው - ሞትና ወደ ሞት አፋፍ የሚያደርስ ወሳኔ፡፡ ስልጣናቸውን በመጋረር የቆመው የእናታቸው ልጅ ቢሆን እንኳን የሞትን ፅዋ እንዲጎነጭ ከማድረግ ወደ ኋላ የሚሉ ግለሰብ አይደሉም፡፡ በእርሳቸው ዕይታ፣ የተለየ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያራምድን ግለሰብ ፍርድ ቤት ማቅረብ "ጊዜ መፍጀት" በመሆኑ፤ የመጨረሻውን ቅጣት ወይም ወደ መጨረሻው ቅጣት አፋጥኖ የሚያደርሰውን ወሳኔ ማስጠት ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ፡፡"… አዎ! ዛሬ ለአስመራው አምባገነን ቡድን የማስጠንቀቂያ ደወል ያቃጨሉት የዴሞክራሲና የፍትህ ፋኖዎች ፍፃሜ የሚወሰነው በአቶ ኢሳያስ ተፈጥሮአዊ ባህሪ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው—ነገረ ስራቸው "ሰሚ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ" እንዲሉት ዓይነት ነውና። ቸር እንሰንብት።